መጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ/ም

ለዶክተር ገላውዴዎስ፤

የማክበር ሰላምታ አቀርባለሁ።

“መንከባከብና ማስወገድ ያለብን ባህሎች” የተሰኘውን መጽሐፍህን አነበብኩት።

ወቅታዊና እጅግ ጠቃሚ የሆነውን መጽሐፍህን በማበርከትህ አድናቆቴን ለመግለጽ እወዳለሁ። ተምሬበታለሁ።

መጽሐፉ፤ ለዘመናት ስለ ቆዩት ባሕሎች ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ ስለሚያስፈልጉንም፤ ለምሳሌ፤ ተፈጥሮን ስለ ማድነቅ፤ ስለ የፖለቲካ ባሕል፤ ወዘተ. ጠቃሚ ግንዛቤ እንደሚያስገኝ አምናለሁ።

በመሠረቱ፤ ባሕልን እንዳለ መቀጠል ሳይሆን፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ካለው ሁኔታ ጋር በማነጻጸር የሚበጀውን የመጠበቅ የሚጎዳውን የማስወገድ ሀሳብህ ለሕብረተሰባችን የሚጠቅም ይመስለኛል።

በተጨማሪ፤ ስለ ባሕል ጉዳይ ጥልቅ እውቀት ባይኖረኝም በተራ ግንዛቤዬ የሚከተሉትን ነጥቦች አቀርብልሀለሁ፤

1ኛ/ መጽሐፉ፤ አማርኛ ለማያውቁ ወገኖቻችንና ለሌሎችም ዜጎች ስለሚጠቅም በእንግሊዝኛም ቢዘጋጅ ጥሩ ይመስለኛል።

2ኛ/ ገጽ 90 ላይ “ግጭትና አፈታቱ” በማለት ጠቀስ አድርገህ ያለፍከው ጉዳይ (conflict resolution) በሐገራችንና ውጪ ላለነውም ኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ ትኩረት የሚገባው ይመስለኛል። ያላወቅንበት አንድ ጉዳይ ቢኖር ይኸው ስለሆነ!

3ኛ/ ስለ ግዝረት ስላነሳኸው ጉዳይ፤

(ሀ) የሴት መሰፋት፤ በሐረርጌ አሁንም እየተገበረ ነው።
(ለ) የወንድ መገረዝ፤ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን ለመከላከል መከናወን ካለባቸው ተግባሮች አንዱ መሆኑ ተረጋግጧል። ለምሳሌ፤ የዛምቢያ መንግሥት ለዜጎቹ ወንድ ልጆች እንዲገረዙ እየመከረ መሆኑ ከታማኝ ምንጭ ተገንዝቤያለሁ።

4ኛ/ ውጪ ሐገሮች ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከሚያስፈልጋቸው የባሕል ለውጦች አንደኛው ትዳርን ለማበረታታት ሊኖር ስለሚገባው አስተሳሰብና አደረጃጀት ነው። አቃጣሪ የተሰኘውን አጉል ባሕል በመፍራት ለአቅመ-አዳም የደረሱ ልጆች የሚተዋወቁበት ሥርዓት ባለመኖሩ ምክንያት ብቻ ቆመው ሲቀሩ ይታያል። እኔ ከማውቀው አንድ የሕንድ ቤተክርስቲያን መማር የሚቻለው ሥርዓት፤ እያንዳንዱ ቤተሰብ ስለ ልጁ/ልጅቷ ዋና ዋና ፍሬ ነገሮችን (እድሜ፤ ትምሕርት፣ ሥራ፤

ወዘተ.) ያስመዘግብና ትዳር የሚፈልጉ ቤተሰቦች ያንን ሰነድ እየተመለከቱ ልጆቻቸውን ያስተዋውቃሉ። የሚቀረው የልጆቹ ፋንታ ይሆናል።

5ኛ/ "አምስቱ የእጅ ጣቶች በአንድነት እንጂ በተናጠል መስራት አይችሉም" (ገጽ 7) የተባለው እንዲታሰብበት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ለልዩ ልዩ ጉዳዮች (ለደግም ለክፉም) ከአምስት ባነሱ ጣቶች የምንገልጻቸው ሀሳቦችና የምናከናውናቸው ድርጊቶች አሉ። ለምሳሌ፣ "የሌባ ጣት"፣ ፊርማ፣ ወዘተ።

6ኛ/ መጽሐፍህ (ባንተው አማካኝነትም ሆነ በልጅህ) የበለጠ ተስፋፍቶ እንደገና እንደሚታተም ተስፋ አደርጋለሁ። በሚቀጥለው ሕትመት፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች እንደምታስብባቸው ተስፋ አደርጋለሁ፣

(ሀ) መታረም የሚገባቸውና አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ ባሕሎች እንዲካተቱ ማድረግ፣

(ለ) የመጽሐፉ ዘገባ አብዘኛውን በግል ግንዛቤ የተመሠረተ በመሆን ፋንታ ለተጨማሪ ጥናት እንዲያመቻች የዋቢ ማስረጃዎችም በጥንቃቄ እንዲካተቱ ማድረግ፣

(ሐ) ምናልባት በሕትመት ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። ነገር ግን በዛ ያሉ የሆሄዎችና የአማርኛ ግድፈቶች አሉ። ለምሳሌ፣ "ሂወት" (ሕይወት)፣ "መሳልል" (መሰላል)፣ "ቀተለ ነብስ" (የተለመደው የአማርኛ አነጋገርም -ነፍሰ-ገዳይ- ልክ አይደለም፣ ነፍስ ስለማይሞት! ሰው-ገዳይ ማለት ይሻል ይሻል ይሆነ?)፣ "በነገር ይቅደም የሰው መብት" (freedom of Expressionን ለመተርጎም ከሆነ 'ሐሳብን የመግለጽ መብት' ማለት ይሻል ይሆን?)፣ "ን" አስቸግራለች!

ለማንኛውም፣ ከላይ የገለጽኳቸው ጥቃቅን ነጥቦች፣ የመጽሐፉን ከፍተኛ ጠቃሚነት ስለማይቀንሱ፣ ልባዊ ምሥጋናዬን በትሕትና እገለጻለሁ።

ኪዳኔ ዓለማየሁ።